# ስለ COVID-19 ክትባት ትራንስክሪፕት በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

ምናልባት አሁን ስለ COVID-19 ክትባቶች ብዙ መረጃዎችን እየሰሙ ነው። COVID-19 ክትባቶች እንዴት እየተሰሩ እንዳሉ አንዳንድ የተለመዱ ጥያቄዎችን ለመመለስ ፈለግን።

## የCOVID-19 ክትባቶች በፍጥነት እየተሰሩ ያሉት እንዴት ነው?

አብዛኛውን ጊዜ፣ ከፍተኛ መጠን ያለው ክትባት ከመሰራቱ በፊት ክትባቱ ደህንነቱ የተጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ይመረመራል። በተከሰተው ወረርሽኝ ከፌዴራል መንግሥት በሚመጣው ገንዘብ ምክንያት ሳይንቲስቶች ሁለቱንም በአንድ ጊዜ እያከናወኑ ይገኛሉ። ምርመራ የተደረገባቸው እና ደህንነታቸው የተጠበቁ ክትባቶች ብቻ ጥቅም ላይ ይውላሉ።

## ክትባቶቹ እንዴት እየተሞከሩ ነው?

በሙከራ ላይ ያሉ የተለያዩ የCOVID-19 ክትባቶች አሉ። እነዚህ ምርመራዎች ክሊኒካዊ ሙከራዎች ተብለው ይጠራሉ። እያንዳንዱ ክትባት ከአንድ በላይ ምርመራዎችን ማለፍ አለበት። በመጀመሪያ፣ ክትባቱ በትንሽ የበጎ ፈቃደኞች ቡድን፣ ከዚያም በመቶዎች የሚቆጠሩ፣ ከዚያም በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ላይ ይሞከራሉ። ለCOVID-19 ክትባት ሙከራዎች ፈቃደኛ ሰዎች ከብዙ የተለያዩ ማህበረሰቦች እና ቦታዎች የመጡ ናቸው። ይህ ሌሎች ክትባቶችን ለመፈተሽ የምንጠቀምበት ተመሳሳይ ሂደት ነው።

## ክትባቶቹ እንዴት ይፀድቃሉ?

ሁሉንም ምርመራዎች ያለፉትን ክትባቶች የሕክምና ባለሙያዎች ቡድን የምርመራ ውጤቶችን እና ክትባቱን ከወሰዱ በኋላ ሰዎች ምን እንደተሰማቸው ይመለከታሉ። ክትባቱ የሚሰራ እና ደህንነቱ የተጠበቀ ከሆነ ይፀድቃል። ለCOVID-19 ክትባቶች የክትባት ደህንነት መረጃን የሚገመግሙ እና ምክሮችን የሚሰጡ ብዙ የሳይንስ እና የባለሙያ ቡድኖች አሉ። ለሰዎች የሚሰጡት የጸደቁ ክትባቶች ብቻ ናቸው።

## መጀመሪያ ክትባቱን የሚወስደው ማነው?

የCDC ብሔራዊ አማካሪ ቡድን መረጃውን በመመልከት በመጀመሪያ ክትባቱን ማን መውሰድ እንዳለበት ምክሮችን ይሰጣል። ለCOVID-19 ከፍተኛ ተጋላጭነት ያላቸው ወይም በCOVID-19 በጣም ሊታመሙ የሚችሉ አንዳንድ ቡድኖች በመጀመሪያ ክትባቱን ያገኛሉ። ሚኒሶታ በጤና ፍትሃዊነት ላይ በማተኮር ክትባት ለሁሉም ሰው ፍትሃዊ ሆኖ እንዲቀርብ የሚያግዙ የባለሙያዎች ቡድን አላት።

ብዙ ክትባት በሚሰጥበት ጊዜ ብዙ ሰዎች ክትባት መውሰድ ይችላሉ፣ ነገር ግን ለሁሉም ክትባት ከመኖሩ በፊት ብዙ ወራትን ይወስዳል።

ስለ COVID-19 ክትባት የበለጠ መረጃ ለማግኘት የጤና መምሪያውን ድረ ገጽ ይጎብኙ።

Minnesota Department of Health
Communications Office
PO Box 64975
St. Paul, MN 55164-0975
651-201-4989
health.communications@state.mn.us
www.health.state.mn.us

11/09/20 (Amharic)

*To obtain this information in a different format, call: 651-201-4989.*